# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ወዝአደር፣ገበሬ፣ነጋዴ፣ወታደር፣ምሁር—
መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቀደም፡፡

ቁጥር 37 ቀን 25/5/68

## የት ደርሰናል?

መግቢያ፡—

የዛሬ ሁለት ዓመት፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ፈጽሞ ታይቶ የማይታወቅ አይነት ሰፊ ህዝባዊ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ፈንድቶ አገሪቱን ከዳር እስከዳር አጥለቀለቃት፡፡ይህ እንቅስቃሴ መሪ መደብ ቢኖረውም መሪ ፓርቲ አልነበረውም፡፡ይህም የሆነው ካገሪቱ የታሪክ እድገት የተነሳ ነበር፡፡ ያገሪቱ ነባራዊ /ኦብጀክቲቭ/ ሁኔታ —ማለትም የሰፊው ህዝብ የኑሮ ሁኔታ፣ ቁስአካላዊ መሰረቱ— ለአብዮት የበሰለ ሆኖ ሳለ፣ የንቅናቄው ደረጃ ግን በዚያው መጠን ወደኋላ የቀረ ስለነበር ነው፡፡

የንቅናቄው መሪ መደብ የነበረው የንኡስ ከበርቴው መደብ ነው፡፡አሁንም እንደዚያው ነው፡፡ የዚህ መደብ የግራ ክንፍ፣ ይህ፣ ዛሬ በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ''ፋሽስታዊ'' የሚለው ክፍል እራሱ ጭምር፣ በዚያን ጊዜ ይህንኑ ዛሬ የሚያወግዙን ወታደር የመንግስትን ስልጣን እንዲይዝ በተቻለው ሁሉ መንገድና ቋንቋ ገፋፍቶት እንደነበር ይታወሳል፡፡ለማንኛውም፣ሰፊው ህዝብ በትግሉ ያለፈውን ስርአት መሰረት ሲያናጋ በህዝብ ስምና ለህዝብ የቆመ ምንም አይነት ድርጅት አልነበረም፡፡በዚህም ምክንያት፣ ከገዥ መደብ እጅ የተፈለቀቀችው ስልጣን ለትንሽ ጊዜ በአየር ላይ ከተንሳፈፈች በኋላ፣ በዚያን ጊዜ ታጥቆ የነበረው ወታደር መጀመሪያ ለህዝብ የቆመ መስሎ ብቅ በማለት፣ በኋላም የሰፊውን ህዝብ መሰረታዊ መብቶች በመገፈፍ ለጊዜው ''ጠባቂ'' ያጣችውን ስልጣን ያዘ፡፡በዚያን ጊዜ ይህን ሊቋቋም የሚችል ሌላ የተደራጀ ሃይል አልነበረም፡፡የወታደሩ ስልጣን መያዝ በዚያን ጊዜ ከነበረው የሰፊው ህዝብ አለመደራጀትና አለመታጠቅ የመጣ አጋጣሚ ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ እንቅስቃሴ እየጋደቀና እየተነሳ፣ የዚህን እንቅስቃሴ መሪነትም በቀላ ጉደል የያዘው ወታደራዊ ደርግ እየተደናበረ፣ አንዴ ወደ ቀኝ አንዴ ወደ ግራ እያጋደለ፣ ይኸው እስከዚህ መጥተናል፡፡ለሰፊው ህዝብ ትግል ሰፋፊ ጎዳናዎችን የሚከፍቱ እርምጃዎች የተወሰዱባቸው ወቅቶች ነበሩ፤ የሰፊው ህዝብ ትግል በየቦታው በፀረአብዮት አመጽ የተደመሰሰበትና በህዝብ ላይ አሰቃቂ ወንጀሎች የተፈፀሙባቸውም ወቅቶች ነበሩ፡፡ሆኖም፣ ማንም ሃቀኛ ተራማጅ በቀላሉ ሊገምት እንደሚችለው ሁሉ፣ የነዚህ ሁለት አመቶች አጠቃላይ ውጤት ሲታይ፣ አዝማሚያው ወደ ግስጋሴ፣ ወደ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱ አቅጣጫ የሚያመራ ሆኖአል፡፡

የተነሳሳነው የየካቲትን እንቅስቃሴ እድገቶችና ውድቀቶች በዝርዝር አቅርበን ሚዛኑን ለማሳየት አይደለም፡፡ይህ ወደፊት መደረግ የሚገባው ነገር ነው፡፡አሁን ግን አንዱን ጥያቄ መመለስ ይኖርብናል፡፡በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱ ጉዳና ላይ የት ደርሰናል? በዚህ አብዮት ጉዳና ላይ አሁን ዛሬ የተደቀኑት ችግሮች ምን ምን ናቸው? የቅርብ ጊዜውስ አዝማሚያ ወዴት ነው? እነዚህንና ሌሎችንም መሰል ጥያቄዎች በሚገባ ካልመለስን የአለቱን ተግባራችንንም በሚገባ ለመወሰንና ለመፈፀም አይቻልም፡፡ስለዚህም፣ ከዚህ በታች ባጭር ባጭሩ ያገሪቱን ሁኔታና የኢትዮጵያን ተራማጆች ተግባር ለማቅረብ ሞክረናል፡፡በነዚህ ነጥቦች ላይ ሰፊ ውይይት እንደሚደረግና ሂሶች እንደሚቀርቡለት ሰሕድ ምኞቱን ይገልፃል፡፡

### 1. የኢትዮጵያ ገጠር ሁኔታ

በገጠር ያለው ሁኔታ ባሁኑ ሰአት በሰሜንም ሆነ በደቡብ፣ የአድሃሪ ሃይሎችን መጠናከር ያሳያል፡፡በሰሜን፣ በቤገምድርና በጎጃም የቀድሞዎቹ ጭቃሹሞችና ነጭለባሾች በነጋ ተገኘ ስሮች ተገፋፍተው ገበሬውን አሰምፀውታል፡፡ስለዚህም በአሁኑ ወቅት ወታደራዊው መንግስት ከገበሬው ከራሱ ጋር ለመዋጋት ተገዶአል፡፡በትግራይም የመንገሻ ስዩምና ሌሎችም ከኤርትራ ግንባሮች ጋር የተያያዙ

ጥቂት ቡድኖች እንዳስቸገሩት ናቸው፡፡ከዚያም የሀንፍሬ አሊ ሚራህ አድሃሪ ''የአፋር ነፃ አውጭ ግንባር'' አለ፡፡እላይ በጠቀምነው መሰረት፣ እነዚህ አድሃሪ ሃይሎች አሁን እንደሚሞክሩት ሁሉ ከተባበሩና አንድ ፀረአብዮታዊ ግንባር ከፈጠሩ፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ እንቅስቃሴም የነርሱንም ፈተና ማለፍ ይኖርበታል፡፡ጥያቄው እንግዲህ ሰፊውን ህዝብ አንቀሳቅሶ በዚህ ትግሉ የሚመራው ሃይል በቅርቡ ሊፈጠር ይችላል ወይ ነው፡፡

በሰሜን ብቻ ሳይሆን በደቡብ ኢትዮጵያም በሲዳሞ፣ በባሌ፣ በከፋ አድሃሪ ሃይሎች እየተጠናከሩ ናቸው፡፡የነአበራ ዎልቶትና የሲዳሞው ፖሊስ ዋና አዛዥ አሁን ባሉበት ቦታ መቆየት በኬንያ ያሉትን የነመንገሻ ስዩምን ደጋፊዎች ያግዛል፡፡የመገናኛ መስመር ይፈጥርላቸዋል፡፡እነዚህ ሁለት አድሃሪዎች በህዝቡ ላይ የፈፀሙዋቸው አሰቃቂ ፍጅቶች እየታወቁ፣ በዚያው ሆነው የደቡቡን ነፍጠኛ ፀረአብዮታዊ ድርጅት እንዲያጠናክሩ መደረጋቸው፣ ሰንቶ ከራሱ ከደርጉ ውስጥ ደጋፊዎችና አበረታቾች እንዳሉዋቸው ያሳያል፡፡በባሌም ሁኔታው ከሲዳሞው የተለየ አይደለም፡፡አስተዳዳሪው ከሶማሊያ ሰርገው የገቡትን ቡድኖች ለመቋቋም ደሃውን ገበሬ በማስታጠቅ ፈንታ ከቀደሞ የመሬት ከበርቴዎች ጋር ይደለታል፡፡አንዳንዶች እንደሚሉትማ ከሆነ ሃይለማርያም ሌንጩ የራሱን መንግስት በባሌ እንደቋቋመ ሊቆጠር ይችላል፡፡አድሃሪ፣ ፈላጭ ቆራጭ፣ በብዙ ዘማቾችና በሌሎችም ተራማጆች ላይ ወሰን የሌለው ወንጀል የፈፀመ ሰው እንደሆነ ይነገርለታል፡፡የከፋ አስተዳዳሪና ቢሮክራሲም እንደዚሁ በክፍለ ሃገሩ አድሃሪ ፈላጭ ቆራጭነትን መስርቶአል፡፡

የደቡቡን ፀረአብዮት እንቅስቃሴ አድሃሪ የደርግ አባሎች እራሳቸው ከጥቂት ወራት በፊት አጠናክረውት ተመልሰዋል፡፡የተባሉት የደርግ አባሎች በሃረርጌ፣ በሲዳሞና በሌሎችም ቦታዎች ከመሬት ከበርቴውና ከፖሊስ ጋር በመሻረክ ብዙ የገበሬ ማህበራትን አፍርሰው ነበር፡፡እነዚህ አድሃሪዎች ያጠናከሩት ፀረአብዮት አሁንም አለ፡፡

በዚያ በኩል ያለው ሁኔታ ትንሽ የተሻሻለ የሚመስለው ''የገበሬዎች ማህበር ማደራጃና ማጠናከሪያ አዋጅ'' ከወጣ በሗላ ነው፡፡የዚህ አዋጅ አጠቃላይ ይዘት አብዮታዊ ሆኖ ሳለ፣ ባንዳንድ አንቀጾቹ፣ በተለይም የፍርድ ሸንጎዎችን ስልጣን በሚመለከተው በኩል፣ ግልጽ ስላልሆነ፣ ፖሊስና ጠቅላላው የገጠር ቢሮክራሲ አዋጁን እንዳሻቸው እየተረጎሙ አሁንም ሰፊውን ህዝብ በመጨቆን ላይ ናቸው፡፡የገጠርን መሬት የህዝብ ያደረገው አዋጅ ከስራ ላይ ሲውል በሚሞክርበት ጊዜ ብዙ መሰናክሎችን እንዳገኘ ሁሉ፣ይህኛውም አዋጅ ኪሩቅ በብዙ ገጠሮች ብዙ ችግሮች አጋጥመውታል፡፡

አዋጁ ባጠቃላይ ይዘቱ አብዮታዊ ነው ብለናል፡፡ይሁንናም እንደማንኛውም ይህ መንግስት እንደሚያወጣው አዋጅ ሁሉ፣ አብዮታዊም ቢሆን፣ ከስራ ላይ በትክክል የመዋሉ ጉዳይ አጠራጣሪ ነው፡፡ አዋጁ የገበሬዎች ማህበር ተግባርና ስልጣን በሚለው አንቀፁ፣ ''የፊውዳሊዝምን ስርአትና የኢምፔሪያሊዝምን ተጽእኖ ለመደምሰስ በሚደረገው ትግል እንዲሳተፍ የአርሶአደሩን ርእዮተ አለም የህብረተሰባዊነት ፍልስፍና ለማነጽ'' ይላል፡፡የአገልግሎትና የአምራቾች የህብረት ስራ ማህበራት ''አላማ፣ ችሎታና ተግባር'' የሚሉት አንቀጾች በያዙአቸው ነጥቦች ውስጥ፣ ''ለማያቋርጥ መሻሻል፣ ለአንድነትና ለዲሞክራሲያዊ መብቶች መታገል፣... ግና ችግርንም የብዝበዛ አይነቶች ቀስ በቀስ ከገጠር ለማጥፋት የመታገልና ከማንኛውም አይነት ብዝበዛ የመገታት፣ የማህበራቱን የፖለቲካ ንቃት ከፍ ለማድረግ የማያቋርጥ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የማካሄድ፣ ወዘተ.'' የሚሉ አሉ፡፡እነዚህና የመሳሰሉት አንቀጾች ያዋጅ አውጭዎችን ቀና ምኞት ከማሳየት በስተቀር፣ ባሁኑ ሰአት፣ አንድም ሰፊውን ህዝብ የሚያንቀሳቅስ አብዮታዊ ፓርቲ በሌለበት ጊዜ፣ በትክክል ከስራ ላይ ሊውሉ አይችሉም፡፡እንዲያውም፣ ከላይ እንደተጠቆመው ሁሉ፣ የገጠር ቢሮክራሲና ፖሊስ በተቻለው መንገድ ሁሉ አዋጁን በማደናቀፍ ላይ ይገኛል፡፡

ከአዋጁ ተሰፋ ሊጣልባቸው የሚችሉ አንቀጾች ''አብዮታዊ የአስተዳደርና የልማት ኮሚቴዎችን'' የሚመለከቱት ናቸው፡፡የነዚህን ውጤት የሚወስነው የዘማቾች፣ የአዝማቾች፣ የገበሬ ማህበራት መሪዎችና የመሬት ይዞታ ሰራተኞች ተባብሮና ተግባብቶ መስራት ነው፡፡እንደዚያም ሆኖ ግን የገበሬዎች የደህንነት ጥበቃ ቡድኖች እስካልታጠቁ ድረስ የነዚህም ኮሚቴዎች ስራ አስቸጋሪ እንደሚሆን ለመገመት ይቻላል፡፡

የሆነው አይነት መሰናከል ቢኖርባቸውም የኢትዮጵያ ገበሬዎች በነዚህ አዋጆች መሰረት እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ ለማድረግ መታገል ያስፈልጋል::ስለዚህም፣ አሁንም የገበሬውን የፖለቲካ ንቃት ከፍ በማድረግ በሁሉም ሊረዱ የሚችሉት ዘማቾች ናቸው::አንዳንዱ የበግ ለምድ የለበሱ አድሃሪዎች እናጁ በገጠር ''ፋሽዝምን ያስፋፋል'' በማለትና ስናው ተግባራችን ደርጉን ገልብጦ ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስትን ማቋቋም ነው'' በማለት፣ ዘማቹ ወደገጠር እንዳይመለሱና ማንኛውንም መስዋእት ሳይፈራ ከሰፊው ህዝብ ጎን ተሰልፎ እንዳይታገል ለማድረግ ሲጥሩ ይታያሉ::እነዚህ የገጠሬው ህዝብ ትግል እንዳይገፋ፣ ገበሬው ከቢሮክራሲውና ከፖሊሱ ጋር በሚያደርገው የእለት በእለት ተጋድሎ አጋርና መሪ እንዲያጣ፣ እጅ እግሩን ታስሮ ለአድሃሪዎች እንዲሰጥና ትግሉ እንዲደመሰስ የሚያገዙ፣ አጋዥ አሳጋቢ፣ የነመንገሻ ሰዎ — ነጋ ተገኝ አጋዞች ናቸው::የሸጭ ደራሲ በተከከለ እንዳመለከተው ሁሉ እዚሁ በየከተማው ''ፋሽስት፣ ፋሽስት'' እያሉ እነአለጋጋ ራሽን በጨበጠ መንገዱ የሚረዱ አድሃሪዎች ናቸው::

በዘማችነት በገጠር ተሰልፈው የነበሩትና አሁንም የተሰለፉት የኢትዮጵያ ወጣቶች ለሰፊው ህዝብ ደህንነት ሲሉ ብዙ ስቃይን ተቀብለዋል::የተረሸኑ፣ የተገረፉ፣ ኢሰብአዊ ስቃይ የተቀበሉ ብዙዎች ናቸው::ነገር ግን በማንኛውም ህብረተሰብ ውስጥ ምንም መስዋእት የሌለበት ''ንፁህ አብዮት'' ተደርጎ አያውቅም::እነዚያን ህይወታቸውን ለሰፊው ህዝብ የሰጡትን ወጣት ሰማእታት የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ሲያስታውሳቸው ይኖራል::ደማቸውንም ሳይበቀልላቸው እንደማይቀር ጥርጥር የለውም::ስለሆነም፣ በኛ አስተያየት፣ የጊዜው የዘማች ተግባር እነዚያ ጓዶቹ ይዘውት የወደቁበትን የአብዮት ባንዲራ አንስተው ትግላቸውን መቀጠል፣ ማንኛውንም መስዋእትነት ሳይፈሩ ቆርጠው ወደፊት መራመድ ነው እንጂ፣ ያለአብዮታዊ ትግል ሊመጣ የማይችለውን የ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስትን''ተአምር መጠበቅ አይደለም::

የገበሬ ማህበራትን ለማደራጀትና ለማጠናከር የወጣው አዋጅ ብዙ ጉድለቶች ቢኖሩበትም፣ አብዮታዊ የሆነ ፓርቲ በሌለበት በኢትዮጵያ ሁኔታ የአዋጁን አብዮታዊ ይዘት ሙሉ በሙሉ ከስራ ላይ ለማዋል እንደማይቻል የታወቀ ነገር ቢሆንም፣ ሰፊው ህዝብ ከቀደሞው ስርአት አውታሮች ጋር በሚያደርገው ተጋድሎ የሚያገዙት አንቀፆች አሉት::ስለዚህም የሃቀኛ ተራማጆች ትግል እነዚህን አንቀፆች ማጠንከርና የገጠሩን ህዝብ ደረጃ በደረጃ ወደብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱ ግብ ለማቅረብ መሆን አለበት::

## 2. የከተሞች ሁኔታ

በከተማ ያለው ዋናው ፀረአብዮታዊ ሃይል የቢሮና አቀባባይ ከበርቴው ነው::በተለይ፣ የቢሮ ከበርቴው ባሁኑ ሰአት የልብ ልብ ተሰምቶት በፊት ይንቀጠቀጥለት የነበረውን ደርግ አሁን ከመጤፍ አይቆጥረውም፤ ያሾፍበታል፤ ያወናብደዋል::በተረፈ ደግሞ ከነመንገሻ ሰዎ ድርጅት ጋር፣ ከኢምፔሪያሊዝምና በደርግ ውስጥም ካሉ አድሃሪዎች ጋር ውስጥ ውስጡን ይደራጃል፣ ያሴራል::

ደርግ የፈለገውን ያህል ተራማጅ አዋጅ ቢያወጣ፣ የመንግስቱን አውታሮች ከላይ የጨበጠው ከፍተኛ የቢሮ ከበርቴ በቦታው እስካለ ድረስ፣ አብዮታዊ እንቅስቃሴው ምንም ያህል አይራመድም:: የቢሮ ከበርቴው ሻጥር /ሳቦታዥ/ የሚሰራበት ብዙ መንገድ አለው::እነዚህን መንገዶች የመንግስቱ ጋዜጦች-ጥምር ሰሞኑን በሰፊው ሲያስረዱ ስለነበር እዚህ ላይ አንመለስባቸውም::ይልቁንስ ከሁሉ አደገኛ የሆነው የቢሮ ከበርቴው ፀረአብዮታዊ ድርጊት ከኢ.ዲ.ዩ/የነመገሻ ሰዎ ፓርቲ/ ከኢምፔሪያሊዝም ጋር መደለቱና ከማሴር ፀረአብዮታዊ ሁኔታን በድርጊት ለማዘጋጀት ማለፉ ነው::ኢምፔሪያሊዝም በድርቅ እርዳታ፣ በኢኮኖሚ እርዳታ፣ በብድር፣ ኤክስፐርት በማቅረብ፣ ወዘተ. አሁንም ቢሆን የሚሰራው ከቀደሞው የቢሮ ከበርቴ ጋር ነው::ይህኛው በተቻለው ዘዴ ሁሉ ያንኪዎችና ሌሎችም ኢምፔሪያሊስት አገሮች በሰፊው፣ ከቀደሞው በበለጠ ሁኔታ ወዳገሪቱ እንዲገቡ ያደርጋል::

የቢሮ ከበርቴው አንዱ አይናውጣ ሻጥር የሚታየው በስራና ቤቶች ሚኒስቴር ድርጊቶች ነው:: የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች አዋጅ ብዙ ጉድለቶች እንዳሉት ይታወቃል::ቢሮክራሲው በነዚህ ጉድለቶች በሚገባ ይጠቀማል::ለተጋረጡት አድሃሪዎች እርዳታ የሚሆኑ ሰፊውን ጭቁን ህዝብ ደግሞ በደርጉ ላይ የሚያስነሱ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል::በህትረት ስራ ማህበራት ተግባር ውስጥ እየገባ

ከላይ እንደየሁኔታው ፀረ ዲሞክራቲክ ትእዛዞችን ያስተላልፋል::በዚህ መንገድ የየቀበሌው ነዋሪዎች የሃይለስላሴ ዘመን ይሻለን ነበር ከሚሉበት ደረጃ ያደርሳቸዋል::በአንዳንድ ምክንያት የቤት እጥረት እንዳለ፤ እንደዚሁም ብዙ ወዛደሮች በዚሁ ምክንያት ስራ እንዳጡ እያወቀ፤ ለቤቶች ስራ የተመደበው ገንዘብ ካሁኑ ከስራ ላይ ውሉል እንዳይዞር በረቀቀ ጥናቶችና ''በቾገሮች'' ትንተና ጊዜው እንዲያልፍ ያደርጋል::ጊዜው እያለፈና ሁኔታው እየባሰ ሲሄድ፤ አካባቢው ለፀረ አብዮት እርምጃ እንደሚያመች የቢሮ ከበርቴው በደንብ ያውቃል::በተጠበጠ መንገድ አነጋገሸ ሰውን ያገዛል ማለት ነው::

የከተሞች የህብረት ስራ ማህበራት በመቀላቀሉ ተስፋ ያላቸው ቢሆኑም በአንዳንድ ቦታዎች በሚመረጡ ሰዎችና በሌቦች አመራር ስር በመሆናቸው፤ በሌሎችም ቦታዎች ጉቦ በለመዱ ካድሬዎች ስር በመሆናቸውና የተመረጡት ሃቀኛ የማህበር ሃላፊዎች ስራቸውን ለማከናወን የማይችሉበት ሁኔታ ስለ ተፈጠረ፤ በመፈራረስ ላይ ያሉ አሉ::ደህና ተራማጆችም ያሉባቸው ማህበራት የሚኒስቴሩን አድሃሪ ተጽእኖ በመታገል ብቻ ተወስነዋል::የነዚህ ማህበራት ጉዳ ችግር ከገበሬ ማህበራት ችግር የተለየ አይደለም::የህዝቡን እንቅስቃሴ አቀናብሮ የሚመራ አብዮታዊ ፓርቲ እስከሌለ ድረስ የማህበራቱ የትግል ውጤት ለጊዜው ቢሆን አጥጋቢ ሊሆን አይችልም::በተረፈም ዲሞክራሲያዊ መብቶች እስካሁን አለመኖራቸው ይህንን ትግል ክፉኛ እንዳደናቀፈው በቀላሉ ለመገመት ይቻላል::

የወዛደሩን መደብና ዝቅተኛ የቢሮ ሰራተኞችን ሁኔታ በሚመለከተው በኩል፤ ሲሰማ ባለፈው መስከረም ከመንግስቱ ጋር ከተጋጩ በሁዋላ ማህበሩ እንደፈራረሰ ይታወቃል::የመምህራን ማህበርም እንደዚያው ነው::ባሁኑ ሰአት የወዛደሩ መደብና የንኡስ ከበርቴው መደብ የግራ ክንፍ አብዮቱን በተለያዩ መንገዶች ይመለከቱታል::የፊተኛው ባጠቃላይ ገለልተኛነት ውስጥ የወደቀ ቢሆንም፤ ሁለተኛው ደግሞ አኩርፍአል ለማለት ይቻላል::ባለፈው መስከረም ወታደራዊው መንግስት ደንበር የወሰዳቸው እርምጃዎች የለየላቸው ፋሽስታዊ ወንጀሎች ነበሩ::ይሁንናም፤ የወዝአደሩና የንኡስ ከበርቴው ማህበራት መሪዎች የተባሉትም ንኡስ ከበርቴዎች በቃል ተራማጅ፤ በድርጊት አድሃሪ በሆኑት በኢ.ሀ.አ.ፓ. እና በተመሳሳይ ቡድኖች ድንፋታ ብቻ፤ የሚወክሉአቸውን ድርጅቶች ወደማያዋጣ አጉል ድፍረት /አድቬንቸሪዝም/ አስገብተዋቸው እንደነበር ዛሬ ለሁሉም ግልጽ የሆነ ይመስለናል::ባለፈው መስከረም ድርጊቶች የወዛደሩ መደብና ሌሎችም ሰራተኞች የነበረውን ሁኔታ በደንብ አጥንተው ተገቢውን ትምህርት የሚቀስሙበት ጊዜ የግድ መምጣቱ አይቀርም::ባጭሩ ብቻ፤ ማንም ብው ሊክድ የማይችለው አንድ የማህበራቱ ጥፋት ነበር:— ይኸውም በጉባኤዎቹ ላይ የተደረሱባቸው ውሳኔዎች ለሰፊው አባል ቀርበው በነርሱ ላይ ዲሞክራሲያዊ ክርክር ሳይደረግባቸው፤ መሪዎቹ በፈላጭ ቆራጭነት ከላይ ትእዛዝ መስጠታቸው ነበር::ደርግን ''አንበርክክ'' ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የመንጠቅና ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስትን'' ለማቋቋም የመንግስት ግልበጣን ማድረግን የመሳሰሉ የሞትና የህይወት ጥያቄዎች እንደዚሁ ከላይ በትእዛዝ መልክ መወርወር የማይገባቸው ነገሮች ነበሩ::የመከራው ውጤት በግልጽ እንዳሳየው ሁሉ፤ ይህ ድርጊት የማህበራቱን ጊዜያዊ መዳከም አስከትሉአል::በዚህም መጥፎነቱ በኛ ግምት ለወዝአደሩ መደብ በተለይ ትምህርት አትርፍአል::ለማንኛውም የወዝአደሩን መደብ ጊዜያዊ ገለልተኛነትና የንኡስ ከበርቴውን የግራ ክንፍ ኩርፊያ በዚህ አንፃር ለመረዳት ይቻላል::

አሁኑ ''የሰራተኛ ድርጅት አዋጅ'' ይህንን ሁኔታ ለጊዜው ምንም ያህል አልለወጠውም:: እንደገበሬ ማህበራት ማጠናከሪያ አዋጅ ሁሉ፤ ምናልባትም በበለጠ ደረጃ፤ ይህኛውም አዋጅ ሊታለፉ የማይችሉ ብዙ ጉድለቶች አሉት::ከነዚህ ውስጥ ዋነኛው በአንቀጽ 106፤ ሰራተኛ ክርክር ተጀምሮ ከ50 ቀን በፊት ስራን ሊያቆም እንደማይችል የሚያስታውቀው —በሃይለስላሴ ዘመን 60 ቀን ነበር! —እና የከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመቃወም ስራን ለማቆም አይቻልም የሚለው ነው::ስራን ማቆም የሰራተኛው የመጨረሻ መሳሪያ መሆኑ እየታወቀ፤ ይህንን መሳሪያ በዋላ ጉደል መቀማቱ በፍፁም ተከስል አይደለም::እንዲያውም በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሰራተኛው የስራ ማቆም መብት እንዳለው በቀጥታ በማያሻማ ቋንቋ ማስፈር ያስፈልግ ነበር::በተረፈም፤ በአንቀጽ 9 መሰረት፤ እንደኢትዮጵያ ባለቸው የሰው የስራ ጉልበት ርካሽ በሆነበት አገር፤ አሰሪው ''አግዘርን ካልፈራ'' በየሶስት ወሩ ሰራተኛን የመቀያየር መንገድ አለው::ሰራተኛው ከስራው የሚታገድበትን ሁኔታ የሚዘረዝረው አንቀጽ 14 ባንዳንድ ንኡስ አንቀጾቹ ሰራተኛውን ለአሰሪው አሳልፎ ይሰጣል::......

ዋናው ቁም ነገር ግን አሁንም እንደዚያው እንደገበሬ ማህበራት ሚመናከሪያ አጀንዳ ነው:: አዋጁ ጉድለቶችን ያዘለ ቢሆንም፣ የኢትዮጵያ ገበሬዎችና ሌሎችም ሰራተኞች በአዋጁ አማካይነት ሊደራጁ ይችላሉ::በዚህ በተጋሰነ መብትም በመጠቀም ገበሬዎቹ ድርጅቶችንና ንቃተህሊናቸውን ሊያጠናክሩ ይችላል::እነዚህ ደግሞ በበኩላቸው ለመጭው የመደብ ትግል በይበልጥ እንዲዘጋጁ ያደርጉታል::

አንዳንድ የግራን ለምድ የለበሱ አድሃሪያን የአዋጁን ጉድለቶች ብቻ በመመልከትና እነዚህን አለመጠን በማጋነን፣ ሰራተኞችን እንዳይደራጁ መቃከር መያዛቸው ታውቋል::በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን፣ ሰርቶ አደሩ ህዝብ በገዛ አራሱ የመደራጀትን እድል ካገኘ መደራጀት አለበት::አትደራጁ ብሎ መምከር ፍፁም አድሃሪነት ነው::

እንግዲህ ለማጠቃለል ያህል፣ የከተማችንም ሁኔታ አይነተኛ የሚያደርገው የቢሮክራሲው ሽጥርና ሴራ፣ ከኢምፔሪያሊዝምና ከነመንገሻ ሰዎም ጋር መመሳጠሩ፣ የንዑስ ከበርቴው የግራ ክንፍ ማኩረፉና የገበሬው መደብ ገለልተኛ አቋም መውሰዱ ነው::ቢሮክራሲያዊ መብቶች ተሰጥተው ቢሮክራሲው ካልተጋለጠና ካልተመታ፣ የንዑስ ከበርቴውም መደብ በየፊናው በመደራጀትና ድምፁን በማሰማት ፊቱን ወደአብዮቱ እንዲመልስ ካልተደረገ፣ የገበሬውም መደብ በፍጥነት ነቅቶና ተደራጅቶ ያለበትን ታሪካዊ ሃላፊነት እንዲገነዘበውና በዚያም መሰረት ትግሉን እንዲያፋፍም ካልተደረገ፣ ከነዚሁ ጋር ተያይዞም የሰራተኛው ችግር በፍጥነት ካልተፈታ፣ የኢኮኖሚ ምግባሮች ካልተስፋፉ፣ የከተማችንም ሁኔታ ለፀረአብዮታዊ ቅልበሳ፣ ለነመንገሻ ሰዎችና ለኢምፔሪያሊዝም ስራ አመቺ ይሆናሉ::

## 3. ኤርትራ፣ ጎረቤት አገሮችና ኢምፔሪያሊዝም

በኤርትራ ጦርነቱ ቀጥሏል::በኤርትራ ተዋጊያቹ፣ በወታደሩና በተለይም በሰላማዊው ህዝብ በኩል ብዙ እልቂት አለ::እንደ ሃይለስላሴ ዘመን ሳይሆን፣ ዛሬ በርግጥ የወንድማማቾች ደም በከንቱ ይፈስባል ከሚባልበት ደረጃ ተደርሷል::ጦርነቱ ባንድ በኩል በሁለቱ ህዝቦች መካከል ቂምና ጥላቻን ይበልጥ እየፈጠረ ሲሄድ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እዚህ በሚካሄደው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል፣ ያገሪትንም ሃብት በከንቱ ያባክናል::ይህ ሁኔታ ለኤርትራና ለኢትዮጵያ ህዝቦች የማይበጅ መሆኑን ሰፊው ህዝብ በደንብ ቢያውቀውም፣ ''የኢትዮጵያ አንድነት ፍፁም ነት'' ያሰጋናው ወታደራዊ ደርግና የግንባሮቹ አድሃሪ መሪዎች ለሰፊው ህዝብ ጥንቃት ደንታ ያላቸው አይመስሉም::ስለዚህም፣ በውይይትና በመተማመን፣ በመቀራረብ ወደመፍትሄ ሊያመራ ይችል የነበረው የኤርትራ ጦርነት ዛሬ እየተባባሰ፣ ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉትን ሃይሎችም እየሳበና በነገሩ እንዲገቡበት እያደረገ፣ ይበልጡን አደገኛ እየሆነ ሄዷል::

የዛሬ አመት ተደርጉ የነበረው የግንባሮቹ ትልቅ ጥቃት የተመሰረተው በሚደረባ ግምት ላይ እንደነበረ ግልፅ ይሰይቶአል::ሃይለስላሴ ከወደቀ በኋላና በተለይም በኢትዮጵያ ውስጥ አንዳንድ የግራ እንቅስቃሴዎች ወዲያውኑ በደርጉ ላይ ሲነሱ፣ ለኤርትራ ግንባሮች መሪዎች ደርግ አንድ ሃሙስ የቀረው መንግስት መስሎአቸው ነበር::ምናልባት የአረብ አገሮችም እርዳታ ከዚያ ጥቃት በፊት እንደዚያ እጥፍ ድርብ ሆኖ የመጣው በዚሁ በተሳሳተ ግምት ላይ በመመስረት ባይሆን አልቀረም:: የኤርትራ ግንባሮች ለታገሉባቸው በርከት ያሉ አመታት አመራሩን የያዘው የአድሃሪው ክፍል ነው:: የዚህ ክፍል ግምትና ጥረት፣ ከቀደምትም በውጭ አገር ያሳትሟቸው የነበሩ ጽሁፎች እንደሚያሳዩት ሁሉ፣ ሃይለስላሴ ከወደቀ ኢትዮጵያ ትበታተናለች፣ ስለዚህም ኤርትራ ነፃ ወጥታ የራሷን ባንዲራ የምትሰቅልበት ሁኔታ ይፈጠራል በሚል ትንተና የተጋሰነ ነበር::ይህ የሰፊውን ህዝብ ትግልና ፍላጎት የሚንቅ የተሳሳተ ትንተና ባለፈው አመት በጥር ወር በተግባር ተሞክሮ በሁለቱም ሃይሎች በኩል ትልቅ ፍጅትን እንዳስከተለ ይታወቃል::ድርጊቱ ለማንም አልጠቀመም::የኤርትራ ግንባሮች ባንዲራቸውን አልሰቀሉም::የኢትዮጵያ መንግስትም የኤርትራን ተዋጊዎች አልደመሰሰም::በመሃከል ግን የብዙ ሰላማዊ ሰው ንፁህ ደም በገፍ ፈሰሰ::

በዚህ ባለፈው ባንድ አመት ውስጥ እንደመሬት ላራሹ ያሉ፣ እንደኩባንያዎች መወረስ፣ ወዘተ. ያሉ እርምጃዎች በተወሰዱ ቁጥር፣ የኤርትራ ግንባሮች አድሃሪ መሪዎችም ይበልጡን ወደ ቀኝ እየተገፉ ሄደዋል::በሰህይ ቀይም በለን እንዳመለከትነው ሁሉ፣ እነኦስማን ሳላህ ሳቤ ከአረብ አድሃሪ አገሮች፣ ከነመንገሻ ሰዎም — ነጋ ተገኘና ከነአሊ ሚራህ ጋር ''ወዳጅነት''ን ፈጥረዋል፤ በማጥመር ላይም ናቸው::በነዚህ አድሃሪ መሪዎች በኩል ባሁኑ ሰአት አንድ አይነት ትንተና

ስለ ባህል፣ ምናልባት የሚከተለው ይሆናል፡— የመሬት አዋጅ፣ የኩባንያዎች መወረስ፣ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት መወሰዱና ሌሎችም ተራማጅ አዋጆች በደርጉ ላይ ጠላትን ያበዛበታል፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ይሰባበራል፤ በዚህ ላይ የመጣው ትርምሱና የሰራተኛው ተቃውሞ አለ፤ ስለዚህም ደርግ እየተዳከመ ሂዶ መውደቁ አይቀርም፤ ስለዚህም ባገሪቱ ጠቅላላ ትርምስ ይኖራል፤ ጊዜ የሚሰራው ለኛ ነው፤ የኤርትራን ህዝቦች እስከፈለገን፣ በዚህ አጋጣሚ ''ነፃ እንወጣለን''::

ይህ ሊሆን ይችላል::ግን ደግሞ ሌላ ሊሆን የሚችለም ነገር አለ::ይኸውም የኤርትራ /የኢትዮጵያም/ ሰፊ ህዝብ መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት መቻል ነው::የኤርትራም ሆነ የኢትዮጵያ ሰርቶአደር ህዝብ የሚፈልገው ፍትህን፣ ሰላምን፣ እኩልነትን፣ ነፃነትን፣ ዴሞክራሲን ነው::ሰርቶአደሩ ህዝብ የሚፈልገው የመደብ ብዝበዛና ጭቆና የሚደመሰሰበትንና የብሄረሰቦች፣ የሃይማኖቶች፣ የጾታዎች እኩልነት በህግና በተግባር የሚከበርበትን፣ ማንኛውም ዜጋ ሰርቶ ለማደር ነፃነቱን የሚያገኝበትን ስርአት ለመፍጠር ነው::እነዚህን ጥያቄዎችን ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ሊያሟላ ይችላል ለማለት ሳይሆን፣ በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ያለው አብዮታዊ እንቅስቃሴ በትክክል ''ሲመራ'' ከቻለ /በተራማጆች ላይ የሚወድቅ ትልቅ ሃላፊነት ነው::/ ወደነዚህ ጥያቄዎች መፍትሄም ሊያመራ ይችላል::ይህ ከሆነ ደግሞ አድሃሪያኖችን የግንባሮችን መሪዎች የኤርትራ ሰፊ ህዝብ እራሱ አጋልጦና ለብቻ ነጥሎ፣ የአብዮቱን መቅረዝ እራሱ በመያዝ፣ ትግሉን በትክክለኛው አገባብ አፋፍሞ፣ መብቶቹን ወደማስመለስ፣ ወደእውነተኛ እኩልነትና አንድነት፣ ወደፍትህና ወደእድገት፣ ወደሰፊው ህዝብ ደህንነት ማምራት ከሚችልበት ሁኔታ ሊያደርሰው ይችላል::የዚህ አይነቱ ሁኔታ ሊፈጠር አይችልም ብሎ የሚተው ነገር አይመስለንም::ያም ሆነ ይህ፣ የኤርትራ ጦርነት በአሁኑ አኳሃን ከቀጠለ፣ ሁለቱም ወገኖች ጥያቄውን በሰላም ለመፍታት ካልሞከሩ፣ ሰፊው ህዝብ በከንቱ የሚሰቃይ መሆኑን የኤርትራና የኢትዮጵያ ተራማጆች በደንብ ሊያውቁት ይገባል::

በኤርትራ ግንባሮች አድሃሪ መሪዎች በኩል ያለው ''ትንተና'' ከላይ የጠቀስነው ጠባብ ብሄረተኝነትን የሚያንፀባርቅ አስተሳሰብ ሲሆን፣ በደርጉ በኩል ያለው ደግሞ የዚያኑ ያህል በትምክህት ላይ የተመረኮዘ ''ኢትዮጵያዊ ብሄረተኝነትን'' ያንፀባርቃል::ከዚህ በፊት ተደጋግሞ እንደተነገረው ሁሉ፣ ከመደብ ይዘቱ የተነሳ፣ ደርጉ ከዚህ ከ''ብሄረተኛ'' ርእዮተአለም ሌላ፣ ለምሳሌም የወዛደሩን መደብ አለምአቀፋዊነት /ኢንተርናሽናሊዝም/ ሊያንፀባርቅ አይችልም::ስለዚህም ''በኢትዮጵያ አንድነት ፍፁምነት'' ጠጥብቆ ያምናል::ከስር ቢገለበጥ ይገለበጣል እንጂ ይህችን እምነቱን እስከመቼውም የሚለቃት አይመስልም::ከዚህም የተነሳ፣ ኤርትራን በሚመለከት በኩል፣ እስካሁን ደርጉ በፖለቲካ ፈንታ የጉልበትን መፍትሄ መርጦአል::ይሁንናም፣ አገሪቱ ባለችበት በዛሬው ሁኔታ፣ ዋናው መፍትሄ ፖለቲካዊ መሆን ነበረበት::

ይህንን መፍትሄ በሚመለከት በኩል፣ የሰህድ አቋም የታወቀ ነው::መጀመሪያ ነገር፣ የኢትዮጵያ መንግስት የብሄረሰቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት በይፋ ማወቅ አለበት:: ይህንን መብት ማወቁን በገቢር ለማሳየት የሚያስችሉትን አንዳንድ እርምጃዎችንም ካሁኑ መውሰድ ይኖርበታል::ሁለተኛ ነገር፣ በትግሉ ሜዳ ለሚገኙት ተራማጅ ኤርትራውያን ካሁኑ የሰላም ጥሪ በይፋ አድርጎ ጦርነቱ የሚቆምበትን ሁኔታ ከነርሱ ጋር መወያየት አለበት::የዚህ አይነቱ ውይይት የመጀመሪያ ተግባር ሰላምን ማግኘት ነው::ሶስተኛ ነገር፣ የሰላም ሁኔታ ከተፈጠረ ወዲያ የኤርትራና የኢትዮጵያ ህዝቦች ስለኤርትራ ጥያቄ ሰፊ ዴሞክራሲያዊ ክርክር አድርገው፣ የኤርትራ ብሄረሰቦች የወደፊት እድል በራሳቸው በኤርትራውያን መወሰን ይኖርበታል::ለማንኛውም፣ የመወያያ ነጥቦቹ የሆኑትን ቢሆኑም፣ ጊዜያዊው ወታደራዊ መንግስት በፍጥነት የሰላምን ጥሪ በትግሉ ሜዳ ለሚገኙት ተራማጅ ኤርትራውያን በይፋ ማቅረብ ይኖርበታል::በኛ አስተያየት የፖለቲካው መፍትሄ ቁልፍ ይህ ስለሆነ በዚያ መጀመር ያስፈልጋል::

ይህ እንግዲህ የኤርትራንና የኢትዮጵያን የውስጥ ሁኔታዎች ስንመለከት ነው::ይሁን እንጂ፣ ባሁኑ ጊዜ የኤርትራን ጥያቄ ከነዚህ ሁኔታዎች አንፃር ብቻ መመልከት ትክክል አይሆንም::በተለይም ኢትዮጵያ ባጠቃላይ ሲታይ ወደግራ ማዘንበልን ከጀመረች ወዲህ፣ በዚህ ጥያቄ ውስጥ አያሌ የውጭ ሃይሎችም ገብተውበታል::የነዚህ ሃይሎች በነገሩ መግባትም ጥያቄውን ይበልጥ ውስብስብ አድርጎታል::

አድሃሪ የአረብ አገሮች፣ እንደሳውዲ አረቢያ ያሉት፣ የቀይ ባህርን አካባቢ የአድሃሪዎች ሰፈር ለማድረግ እንደሚፈልጉና፣ ለዚህም፣ በአንድ ጋዜጣ አባባል ''የኤርትራን አረብ ህዝብ'' ትግል ከመቼውም ይበልጥ እንደሚደግፉ በግልጽ ተናግረዋል:: ቀደም ከሃይለሥላሴ ጋር ስምምነት የነበረውና ተራማጆችን የሚጠረጥረው የሱዳኑ ኑሜሪም እንደዚሁ የኤርትራን ገንባሮች ይደግፋል፤ እነመንግሽ ስዎንም ይረዳል::ሶማሊያ ጂቡቲን ለመያዝና ኦጋዴንንም ለመውሰድ ስለምትፈልግ፣ የኤርትራን ገንባሮች ብቻ ሳይሆን ሃገናሪ አሊሚራህንም የምታበረታታ ይመስላል::በዚያው አካባቢ በኦጋዴንና በተለይም በባሌ ፕሮቪንስን —ተንኮል— በመፈፀም ላይ የሚገኙ የታጠቁ ቡድኖች እንዳሉ ይታወቃል::በኬንያ የነመንግሽ ስዎ ደጋፊዎች በመደራጀትና በመጠናከር ላይ እንዳሉ ይነገራል:: የሃይለሥላሴ መንግስት ቀደም የኢትዮጵያን ህዝቦች ለማጋናበድ ''ተከበናል'' እያለ ሲያስጋራና ሲለፍፍ የነበረው ሃሰት ዛሬ በርግጥም በተጨባጭ መልክ የሚታይ ይመስላል::ይህ ሁሉ ሁኔታ የኤርትራን ገንባሮች አድሃሪ መሪዎች የሚያበረታታ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም::መታወቅ ያለበት ግን የዚህ ጠቅላላ ''ርኩስ ወዳጅነት'' አላማ የኤርትራን ህዝብ ከተባለው ''የኢትዮጵያ ኮሎኒያሊዝም'' ነፃ ለማውጣት ሳይሆን፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች የጀመሩትን አብዮታዊ እንቅስቃሴ ለመደምሰስ መሆኑ ነው::

ከዚህ ሁሉ ጋር የሁለቱ ሃያላን መንግስታት ውድድር አለ::ማንም እንደሚያውቀው ኢትዮጵያ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በአፍሪካ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ዋና ምሽግ ነበረች::አሁንም ቢሆን ደግሞ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ባገሪቱ የኤኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የባህልና ወታደራዊ አቋም ላይ ፈጽሞ የማይናቅ ተጽእኖ አለው::ከኛ ዝቅ ብሎ ደግሞ ሶቭየት ህብረት በሶማሊያ ውስጥ በሰፊው ገብታለች::ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በኢትዮጵያ ላይ የነበረውን ያህሉ ቁጥጥር ይህኛው ሃያል መንግስትም በሶማሊያ ላይ ተጽእኖ አለው::በሌላ በኩል ደግሞ ይኸው ሃያል መንግስት በኢትዮጵያ ላይ ከተሰለፉት አንዳንድ የአረብ አገሮች ጋር የጠበቀ ''ወዳጅነት'' አለው::የሁለቱ ሃያላን መንግስታት ውድድር የሚያተኩረው በአፍሪቃ፣ በቀይ ባህርና በህንድ ውቅያኖስ ላይ በመሆኑና ኢትዮጵያም በዚህ ያፍሪቃ ክፍል የያዘችው የስትራተጂ ቦታ ከፍተኛ በመሆኑ፣ የኤርትራም ጥያቄ በዚህ ውስብስብ ሁኔታ ውስጥ መታየት ይኖርበታል::አሁን እንግዲህ በደረስንበት ሁኔታ አሜሪካኖችም አልወጡ፣ ሶቭየቶችም አልገቡ፤ ውስጥ ውስጡን እነርሱ የተስማሙበትን ነገር ለማወቅ ያስቸግራል::...

የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች የራሳቸውን ችግር በራሳቸው ለመፍታት መቻል አለባቸው:: ከዚህ በላይ ስለመፍትሄ ስንናገር ቁልፉ የሚገኘው በትግሉ ሜዳ ላይ ባሉት ተራማጅ ኤርትራውያን ዘንድ ነው ያልነው በዚህ ምክንያት ነው::እንኳንስ እንደነዚህ በብዙ ክር የተሳሰሩ ሁለት ህዝቦች ቀርተው፣ ሌሎችም አፍሪካውያን ቢሆኑ፣ በመካከላቸው የሚነሱትን ችግሮች የውጭ እጅ ሳያስገቡ እራሳቸው በውይይትና በሰላም መፍታት አለባቸው::ይህ ሆኖ ሳለ፣ ወንድማማች ህዝቦችን እርስ በርስ ማስጨፍጨፍ፣ ማራራቅ፣ ለበላይነትም ሲባል የዚህኛው ወይም የዚያኛው ባእድ ሃይል ጥገኛ መሆን አሳፋሪ ብቻ ሳይሆን በሰፊው ህዝብ ላይም የሚፈፀም ትልቅ ወንጀል ነው::ለዚህም ሃላፊዎቹ አንድ ቀን የግድ ይጠየቁበታል::

በበኩላችን የኤርትራና የኢትዮጵያ ሰርቶአደር ህዝቦች ጥቅም አንድ ነው እንላለን::ሰፊው ህዝብ የርስ በርስን መቀራረብና በማንኛውም ነገር የመደጋገፍን፣ የመተባበርና የመተሳሰርን ጠቃሚነት ያውቃል::ስለዚህም፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነትን ይፈልጋል::ይህንን ሃቅ ስለምናውቅ፣ ባሁኑ ሰአት የኤርትራም ተራማጆች አብረውን እንዲሰለፉ ጥሪ እናደርግላቸዋለን::ለኤርትራም ሆነ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ለእኩልነት፣ ለነፃነት፣ ለሰላምና ለእድገት ለሚያደርጉት ትግልና ለሚጠቅማቸው ዘላቂ አንድነት ዋስትና ሊሆን የሚችለው የልዩ ልዩ ብሄረሰቦች ተራማጆች በመደብ ደረጃና በአለምአቀፋዊነት መተሳሰር ብቻ ነው::

## 4. የኢትዮጵያ ተራማጆች አሰላለፍ

የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የተራማጆችን የጠበቀ ህብረትና የወዛደሩን ፓርቲ በፍጥነት መገንባት በሚጠይቅበት ባሁኑ ሰአት፣ በዙ የኢትዮጵያ ''አብዮታውያን'' ተራማጅ አስተሳሰብን በሚያጋጥማቸው ''የህፃንነት በሽታ'' ተለክፈዋል::አንዳንዱ ፋን ሰዎች የተራማጅን በጥቂት ቡድኖች መከፋፈል እያዩ፣ ''እርስ በርስ መበጣጠቃን'' እየተመለከቱ ተስፋ ይቆርጣሉ::ነገር ግን ይህ የእድገት ምልክት መሆኑን የግዱ ማስታወስ ያስፈልጋል::በማንኛውም አብዮት ውስጥ የዚህ አይነቱ የግራ ሃይል መከፋፈል ደጋግሞ ደርሶአል::በግራው ውስጥ ''ግራ'' እና ግራ፣ ማለትም ለአፋቸው የግራ በድርጊታቸው ግን የቀኝ የሆኑ በአንድ በኩል፣ በአፋቸውም ሆነ በድርጊታቸው በርግጥ የግራ የሆኑ በሌላ በኩል አሉ::በኢትዮጵያም የዚህ አይነቱ ሁኔታ ከእለት ወደእለት ይበልጡን ገልጽ እየሆነ ሄደአል::ይህም የግድ ወደአንድ አቅጣጫ ማምራት ይኖርበታል::ሃቀኛው ግራ እየተጠናከረ፣ የውሸትን ግራ እያጋለጠና እየታገለው ይሄድና የሰፊውን ህዝብ ተቀባይነት ያገኛል:: አድርባዩ ''ግራ'' ግን በመጨረሻ የጥቂት አድሃሪያች ፀረአብዮታዊ ቡድን ሆኖ ይቀራል::

ማንም እንደሚገምተው፣ በኢትዮጵያ ግራ ውስጥ ዛሬ ሁለት አዝማሚያዎች እየጠሩ ሄደዋል:: እነዚህም በጋዜጣቸው በሰህድና በ''ግራው'' ጋዜጣ በዲሞክራሲያ ይወከላሉ::በቅርቡ አንዳንዱ የአብዮታውያን ቡድኖች ብቅ ብቅ ማለታቸው ይታወቃል::ጓዳነት፣ ሬቮሉሽን፣ ዐዛ፣ ታጋይ ኢትዮጵያዊት እና የአብዮት ፋና የሚባሉ ጋዜጦች የወጡት በነዚህ ግሩፖች ሲሆን፣ ከጋዜጦቹ ይዘት በቀላሉ ለመገመት እንደሚቻለው ሁሉ፣ በሰህድና በነርሱ መካከል ከዝርዝር ነጥቦች ሌላ መሰረታዊ የመስመር ልዩነት የለም::የኢትዮጵያን ሁኔታ ትንተናና የተራማጆችን ጊዜያዊ ተግባር በሚመለከተው በኩል ከነዚህ ጋዜጦች ጋር ከሙሉ ስምምነት ላይ ልንደርስ እንችላለን የሚል ግምት አለን::ለማንኛውም ሰህድ ከነዚህ ግሩፖች ጋር ሃቀኛና አብዮታዊ ትብብርን ለመፍጠር፣ በግሩፕ ደረጃ በሀሳና በግል ሀሳ ከእርስ በርሳችን እንድንግባባ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ባለፈው ቁጥሩ ጠቅሶአል::

እንግዲህ በኢትዮጵያ ግራ ውስጥ ያሉት ሁለት አዝማሚያዎች በየትኞቹ ነጥቦች ላይ ነው የሚለያዩት?

በመጀመሪያ ነገር የምንለያየው ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት'' በሚለው መፈክር ነው:: ይህንን መፈክር እንዲያውም ለመጀመሪያ ጊዜ ያቀረበው ሰህድ እንደነበር ይታወሳል::ዛሬ ግን ሰህድ ይህንኑ መፈክር በተቻለው መንገድ ሁሉ ይታገለዋል::ይህንንም ለምን እንደሚያደርግ በዝርዝር ለማወቅ የሚፈልገውን አንባቢ ሰህድ ቁጥር 35ን ፈልጉ እንዲያነብ ከመጋበዝ በስተቀር እዚህ ላይ አንመለሰበትም::ባጭሩ ብቻ፣ ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት'' የሚለው መፈክር እራሱ ሃይለኛ ቅራኔን በውስጡ የያዘ ከመሆኑም በላይ፣ ከስራ ላይ ሊውል ቢችልም እንኳን የንኡስ ከበርቴውን መደብ አንዱ ክንፍ ፈላጭ ቆራጭነት በሰፊው ህዝብ ላይ ከማስፈር ሌላ ምንም ፋይዳ አይኖረውም:: ሰህድ የሚያምነው የአለም ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊና ሶሻሊስት አብዮቶች ፍቱንነቱን ባረጋገጡት በ''ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት'' ነው::ይህም የሚመጣው ሰፊው ህዝብ ነቅቶ፣ ተደራጅቶና ታጥቆ በጉልበት በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም፣ እንዲሁም በወኪሎቻቸውና በርዝራዦቻቸው ላይ ድሉን ባረጋገጠ ብቻ ነው::የምንታገለውም ለዚህ አይነቱ መንግስት መምጣት ነው::ምናልባት የኢትዮጵያ አብዮት ጉዳና የተለየና ራሱን የቻለ ሆኖ በርግጥ ''ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት'' አይፈጠር ይሆናል::ለማንኛውም ግን የነዲሞክራሲያ፣ የነመንገሻ ስዩም፣ ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት'' በምንም አይነት የአብዮታዊውን መንግስት ቦታ ሊወስድ አይችልም::

ሁለተኛው የመለያያ ነጥብ የደርግን ባህርይ የሚመለከተው ትንተና ነው::ሰህድ ደጋግሞ እንዳመለከተው ሁሉ፣ ደርጉ የንኡስ ከበርቴውን መደብ የሚወክል፣ በዚህም ምክንያት በጣም ወላዋይ የሆነ፣ ባጠቃላይ ሲታይም አንዴ ወደቀኝ አንዴ ወደግራ የሚያዘነብል ሃይል ነው::በውስጡም የቀኝና የግራ ቡድኖች አሉ::/ቀኝና ግራ ማለት እዚህ ላይ የተደራጁ፣ በምእራብ አገሮች እንደሚገኙት የፓርላማ ፓርቲዎች ማለት አንዳልሆነ ገልጽ ነው::የደርጉ የቀኝና የግራ ክንፎች ያልተደራጁ ከመሆናቸውም በላይ በአባሎቻቸው ብዙ ጊዜ ተለዋዋጭ ሳይሆኑ አልቀሩም::/ ስለዚህም ደርጉ በአንድ ርእዮተአለምና በአንድ የፖለቲካ መስመር ዙሪያ የተሰበሰበ፣ አንድነት ያለው አካል አይደለም:: በዚህም ምክንያት ነው አንዱ ጊዜ በጣም ተራማጅ፣ አንዱ ጊዜ ደግሞ በጣም አድሃሪ ወይም በጣም ግራ ቀደም እርምጃዎችን የሚወስደው::

በዚህ ነጥብ ላይ የዲሞክራሲያ አቋም ይህን ያህልም ግልጽ አልሆነም። ዲሞክራሲያ በደርጉ ላይ አንድ ስም፣ ለምሳሌ ''ፋሽስት ደርግ''፣ ''ፋሽስት ጁንታ'' ወይንም አሁን በጽሁፎቹ ላይ እየፀደቀ የሄደ የሚመስለውን ''የምርጥ መኮንኖች መንግስት'' የሚሉትን ቅጽሎች ከመለጠፍ አልፎ፣ የደርጉን የመደብ ይዘት ለመተንተን የሞከረበት ጊዜ የለም። አልፎ አልፎም የግራና የቀኝ ሃይሎችን የለየበትና የግራው ክንፍ ከርሱ ጋር እንዲተባበር የጋበዘበት ወቅቶች ነበሩ። እንዲያውም ደግሞ በዚያው በአንዱ የዲሞክራሲያ ቅጥር ውስጥ አሳይ ''ፋሽስት ደርግ'' ብሎ እታች ደግሞ ''በደርጉ ውስጥ የቀኝ ሃይሎች እየተጠናከሩ ናቸው'' በማለት በደርጉ ውስጥ ፋሽስቶችንና ሱፐር ፋሽስቶችን ለመለየት የሞከረበት ወቅት ነበር። ባጭሩ፣ ዲሞክራሲያ እራሱ እንደደርጉ ወላዋይ በመሆን፣ ስለደርጉ ባህርይ ውዥንብርን ነዝቷል፤ በመንዛት ላይም ነው።

ሶስተኛ፣ አብዮታውያን ያንዱን መንግስት የመደብ ባህርይ በግድ መለየት ያለባቸው ለትንተና ቅንጦት ሳይሆን፣ ለትግላቸው ይህ አስፈላጊ ስለሆነ ነው። ከዚህ ትንተና በመነሳት፣ ተራማጆች አንድ የተወሰነ አቀራረብ ይኖራቸዋል። ደርግ በርግጥ ፋሽስት ከሆነ፣ ከኢምፔሪያሊዝምም፣ ከነመንግሽ ሰዎም፣ ማለትም ከመሬት ከበርቴዎች ጋር ጥምር የግድ ተባበር፣ ''ፀረፋሽስት ግንባር'' መስርቶ እርሱን መገልበጥ ያስፈልጋል። ደርግ የንኡስ ከበርቴው ወላዋይና ደንባራ ክፍል ከሆነ ደግሞ፣ ተራማጆች በተቻላቸው መንገድ ሁሉ ሊያረጋግጡት መጣር፣ የግራውንና የቀኙን ለመለየት፣ የግራው ከሰፊው ህዝብ ጋር እንዲሰለፍ ለመገፋፋት፣ ጠቅላላው ደርግ ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ያለውን ቅራኔ ለማፋፋም መታገል ይኖርባቸዋል። ደርግ በፀረፊውዳልና /ገና ባይለይለትም/ በፀረኢምፔሪያሊስት አቋሙ፣ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን የሰፊው ህዝብ ወገን መሆኑን ስለሚረዱት ሃቀኛ ተራማጆች በዚህ ባህርዩ በመጠቀም የሰፊውን ህዝብ ትግል ያራምዱታል። ደርግና ሰፊው ህዝብ ባንድነት በዋነኞቹ ጠላቶች በፊውዳሊዝም፣ በኢምፔሪያሊዝምና በቢሮክራሲያዊው ከበርቴ ላይ እንዲረባረቡ ለማድረግ ይታገላሉ እንጂ፣ የመንግስትን ስልጣን ስለያዘ ብቻ ወታደራዊው ደርግም የሰፊው ህዝብ ዋና ጠላት ሆኖ ከነዚያ ሶስት ጠላቶች እኩል መዋጋት አለበት አይሉም። ሰህዱ የፊተኛውን ፖለቲካ አብዮታዊ ሂስ በሚለው አቋም ሲያጠቃልለው፣ ዲሞክራሲያ ግን ሁለተኛውን የተምታታና ዞር ዞርም ፀረአብዮታዊ የሆነውን አቋሙን በአጋጣሚነቱ ሲረጨው ቆይቷል፤ በመርጨት ላይም ይገኛል።

አራተኛ፣ ከዚህ በላይ ያነሳነው የደርግ ባህርይ ጉዳይ፣ በግልጽ እንደሚታየው፣ ከዛሬይቱ ኢትዮጵያ ቅራኔዎች ትንተና ጋር የተያያዘ ነው። በዲሞክራሲያ ''ትንተና'' መሰረት፣ የየካቲት እንቅስቃሴ ያስከተላቸው ታላላቅ ለውጦች፣ ለምሳሌ የዘውዱ አገዛዝ መውደም፣ የሶሻሊዝም የመንግስት መመሪያ ሆኖ መታወጅ፣ የትላልቅ የኢምፔሪያሊስቶች ኩባንያዎች መወረስ፣ በተለይም የገጠር መሬት የህዝብ መሆን፣ የገበሬ ማህበራት ከነችግሮቻቸውም ቢሆን መቋቋም፣ ወዘተ. ባገሪቱ የቅራኔዎች ቅደም—ተከተል ውስጥ ምንም አላስከተሉም። ለነርሱ የኢትዮጵያ ህዝብ ዋና ጠላቶች ፊውዳሊዝም—ኢምፔሪያሊዝም—የደርግ ፋሽዝም ናቸው። ወይንም ደግሞ በፊውዳሊዝም—ኢምፔሪያሊዝምና በሰፊው ህዝብ መካከል ያለው ቅራኔና በደርግና በሰፊው ህዝብ መካከል ያለው ቅራኔ በባህርዩ፣ በአይነቱ፣ አንድ ነው። ይህ የቅራኔዎች ''ትንተና'' ማወናበጃ መሆኑን ሰህዱ በጊዜው አሳይቷል። ማንም የአብዮታዊ ቲዎሪን ሀ ሁ የቆጠረ ሰው በቀላሉ ሊገነዘበው እንደሚችለው ሁሉ፣ ደርግ ባሁኑ ሰአት ከኢምፔሪያሊዝም ጋር በብዙ ሰንሰለቶች የተያያዘ ቢሆንም፣ በሁለቱ መካከል ቅራኔ እንዳለ ግልጽ ነው። ይህም ቅራኔ በይዘቱ በኃይለሥላሴ መንግስትና በኢምፔሪያሊዝም መካከል ከነበረው ይለያል። ይህኛውን /የኃይለሥላሴ መንግስትና የኢምፔሪያሊዝም ግንኙነት/ አይነተኛ ያደርግ የነበረው በሁለቱ መካከል የነበረው አንድነት ወይም መግባባት፣ መቻቻል ሲሆን፣ ያኛውን /ደርግና ኢምፔሪያሊዝም/ ግን አይነተኛ የሚያደርገው የመራራቅ፣ የትግል፣ የመቃቃር አንፃሩ ነው። ስለዚህም፣ ለጊዜውም ቢሆን፣ ይህ ቅራኔ የደርጉንና የሰፊውን ህዝብ መቀራረብ አስከትሎአል፤ ወይም በማስከተል ላይ ነው። ይህም መቀራረብ ነገ ሊፈርስና ወደጠላትነት ሊለወጥ ይችላል፤ ዛሬ ግን አለ። ከዚህም የተነሳ፣ የአብዮታውያን ተግባር በዚህ ጊዜያዊ መቀራረብ በመጠቀም የሰፊውን ህዝብ ዘላቂ ትግል ማዘጋጀትና ማጠናከር ነው። ይህንን በመሳት ደርግን ባሁኑ ሰአት ከፊውዳሊዝም—ኢምፔሪያሊዝም እኩል እንደዋና ጠላት ሰፊውን ህዝብ ጊዜያዊ ወዳጁን አሳጥቶ ለአድሃሪያን አሳልፎ መስጠት ነው።

አምስተኛ፣ ከዚህ ሁሉ የትንተና ልዩነት ጋር ተያይዞ የትግል ዘዴ ልዩነት አለ።ይህንንም ነጥብ ያለፈው አንድ ቁጥራችን በሚገባ ስላብራራው በሰፊው አንመለስበትም።የዴሞክራሲያን የትግል ዘዴ አይነተኛ የሚያደርገው፣ ወረቀቱና ደጋፊዎቹ በግለሰቦች ላይ የሚያደርጉት ዘመቻ፣ በፖለቲካ ክርክር አማካኝነት ደጋፊዎችን በማፍራት ፈንታ በሃሜትና በስም ማጥፋት ያዳማጩን ስሜት ቀስቅስ ''ጀሌ'' ማድረግ፣ ደጋፊው እንዳያስብ፣ እንዳይመራመር፣ የሚሰጡትን መፈክሮችና መመሪያዎች ያላንዳች ጥያቄ እንዲቀበል ማድረግ ነው።ይህም በአብዮታዊ ዲሲፕሊን ቦታ ፋሽስታዊ ዲሲፕሊንን መትከት ነው።ሰሀዴ በበኩሉ በተቻለው መጠን አብዮታዊ ቴዎሪን ለማሰራጨት፣ በውይይትና በክርክር ደጋፊዎችን ለመሳብና እራሱም ለመታረም፣ አስበው፣ አውቀው፣ አሰላስለው፣ የሰሀዴን መስመር የራሳቸው አድርገው የሚታገሉ የነቃ አብዮታውያንን ለመፍጠር ይታገላል።ይህኛው የትግል ዘዴ አድካሚ ነው፤ ረጅም ነው፤ ባንድ ጊዜ ብዙ አጨብጫቢዎችንና ጀሌዎችን የሚያገበስብስ አይደለም።ነገር ግን እውነተኛ የወዛደር ፓርቲን ለመመስረትና በርሱም አማካይነት የኢትዮጵያን ህዝቦች ትግል በቀጥ ለመምራት የሚቻለው በዚህ መንገድ ብቻ መሆኑን ያምንበታል።የሰሀዴ አላማ ጥቂት ጀሌዎችን፣ የቀኛም ሁኑ የግራ፣ አግበስብሶ በነዚህ አማካይነት ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስትን'' በማስመረጥ የመንግስትን ስልጣን በተቻለ ፍጥነት መጨበጥ አይደለም።ቁራጥነትና ትእግስት በተመላበት መንገድ ታግሎ ሰፊው ህዝብ እራሱ በገዛ አብዮታዊ ትግሉ የመንግስትን ስልጣን እንዲጨብጥ ማድረግ ነው።በዚህም ምክንያት የሁለታችን የትግል ዘዴዎች እንደሰማይና ምድር የተራራቁ ሆነዋል።

በመጨረሻም፣ በሰሀዴና በዴሞክራሲያ መካከል ያለው መሰረታዊ ልዩነት፣ ከላይ የተጠቀሱትን ሁሉ የሚያጠቃልለው የርእዮተአለም ልዩነት ነው።በኢትዮጵያ ግራ ውስጥ ዴሞክራሲያ የሚወክለው ደንፊውንና አለሁ አለሁ ባዩን ንኡስ ከበርቴ ነው።ይህ ክፍል፣ በሰፊው ህዝብ ላይ አንዳንድ ጭቆናዎች ሲፈፀሙ ባየ ቁጥር በሃይለኛ ስሜት ይገፋፋና አብዶ ይሆናል።በአጉል ድፍረትና ድንፋታም ህዝቡ ባይደራጅና ሳይታጠቅ እንዲጋፈጥ ይገፋፋል።ሰፊው ህዝብ ጥቂት ድሎችን ባገኘ ቁጥር ደግሞ ''አብዮቱን መምራት ሊቀርብኝ ነው'' በሚል ፍርሃት ተወናብዶ እነዚህን ድሎች ያናንቃል፤ እንዲያውም ድሎቹን በመሸነፍ መተርጎም ይቃጣዋል።በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ጠቅላላውን የአብዮቱን ሂደት ለመገምገምና አዝማሚያው ወዴት እንደሆነ ለማየት ስለማይችል፣ ለማየትም ጥረት ስለማያደርግ፣ ''ትንተናዎቹ'' ከአፍንጫው ርቀው የማይሄዱና በግሊያዊነት /ሳብጀክቲቪዝም/ የተሞሉ ናቸው።ከመጠን በላይ የሆነ ተስፋና ከመጠን በላይ የሆነ ተስፋ መቁረጥም ይፈራረቁበታል።በዚህ መልካቸው ሲታዩ ደርግና ዴሞክራሲያ አንድ ናቸው ለማለት ይቻላል።

ሰሀዴም ቢሆን በድሃው ገበሬና በወዛደሩ፣ በተለይም በዚህኛው ውስጥ ስር እስኪሰድደ ድረስ በንኡስ ከበርቴው ጠባዮች እንደተበከለ ይኖራል።ይሁንናም፣ በተቻለው መጠን በወዛደሩ ርእዮተአለም ለመመራት፣ በትንተናው ሁልጊዜ ከተጨባጭ ሁኔታዎች ለመነሳትና ነገሮችን ከሁሉም ማእዘን ለመመልከት ይጥራል።ማንም ሊከደው እንደማይችለም፣ ሰሀዴ ባቋራጭ የመንግስትን ስልጣን ለመያዝ ሳይሆን ለዘላቂው ህዝባዊ ትግል መቃናት ይታገላል።ለማንኛውም፣ የሚመጡት አመታት በርግጥ በሁለቱ መስመሮች መካከል መለየታቸው እንደማይቀር ፈጽሞ አንጠራጠርም።

## 5. ደርግ፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶች፣ የፖለቲካ ጸ/ቤት

ከዚህ በላይ ባንድ ቦታ እንደጠቀስነው ሁሉ፣ ደርጉ የግራና የቀኝ ክንፎች አሉት።በጠቅላላው፣ ግራ የምንለው የጊዜውን የኢትዮጵያ ሁኔታና የአብዮቱን አቅጣጫ በቀሳ ጉደል ተረድቶ፣ በዚህ አቅጣጫ ግስጋሴ እንዲኖር የሚታገለውን የደርግ አባል ሁሉ የሚይዘውን ክፍል ነው።የቀኝ የምንለው ደግሞ በመደብ ጥቅም፣ ወይንም ከደርግ ውጭ ካሉት ያገርና ባእድ አድሃሪዎች ጋር በመሻረክ፣ ወይንም ደግሞ ሁኔታውን ባለመረዳትና በፍርሃት፣ —ዙር ዙር እነዚህም ሁሉ የመደብን ጥቅም የሚመለከቱ ነጥቦች መሆናቸውን አንረሳም— በጠቅላላው የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ እንቅስቃሴ ወደፊት እንዳይራመድ መሰናከል የሚሆነውን ሁሉ ነው።አንዳንድ ተራማጆች የዚህ አይነቱ የደርግ አከፋፈል መኖሩን ይጠራጠራሉ።ይሁንናም፣ እንኳንስ እንደደርጉ ባለው የሰዎች ቡድን ውስጥ ይቅርና በአንድ ሰው አንጎልም ውስጥ የመደቦችን ትግል የሚያንፀባርቁ የግራና የቀኝ አስተሳሰቦች

እንዳሉ የታወቀ ነገር ነው።እንደዚሁም መደቦች፣ የወዛደሩ መደብ ጭምር፣ የቀኝና የግራ ክንፎች አሉአቸው።ስለዚህም በወዛደሩ እንቅስቃሴ ውስጥ ተደጋግሞ እንደታየው ሁሉ ለዎባሉ የቀኝና ''የግራ'' አድርባይነት የሚባል ነገር አለ።የደርጉ የግራና የቀኝ ክንፎች አሉ ተብሎ እንጂ እነዚህ ክንፎች የለየላቸውና የተደላደሉ ናቸው ማለት አይደለም።ይህ ወደፊት ሊመጣ ይችላል።ለማንኛውም፣ ከጥቂት ወራት ወዲህ የሚወሰዱትን እርምጃዎች ብንመለከት፣ የደርጉ የግራ ክንፍ እንደተጠናከረ ለመገመት ይቻላል።

የሰፊው ህዝብ የዲሞክራሲ ጥያቄዎች እየገፉ መምጣታቸውና በደርጉም ውስጥ ያለው የሃይል ሚዛን ለጊዜው ወደግራው ስለሚያዘነብል፣ ረዥም ላለ ጊዜ ሲጠየቁና ሲጠበቁ የነበሩት ዲሞክራሲያዊ መብቶች በቅርቡ ባይገኙ አይቀሬም ብለን እንገምታለን።የነዚህ መብቶች መለቀቅ በየካቲቱ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ታሪክ ውስጥ፣ ከ''መሬት ላራሹ'' በማያንስ መንገድ፣ አዲስ ምእራፍን ይከፍታል።

ዲሞክራሲያዊ መብቶች በትክክል ከስራ ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ለመፍጠርና ሰፊው ህዝብ በፍጥነት የፖለቲካ ንቃትን እንዲያገኝ፣ እንዲደራጅና እንዲታጠቅ ለማድረግ የሚያግዝ የፖለቲካ ጽህፈት ቤት በደርጉ ስር እንደተቋቋመ ያደባባይ ምስጢር ሆኗል።ይህ ጽህፈት ቤት በርግጥ ከላይ የተጠቀሱትን ተግባሮች የሚያከናውን እንጂ በከተማ እንደሚወራው ''የደርጉን ፓርቲ'' ለማቋቋም የተፈጠረ ካልሆነ፣ ስህዴ አባጡን በመሰረቱ ይደግፈዋል።ለማንኛውም ግን፣ ጋዘጦችን አቋም ከመውሰዱ በፊት የጽህፈት ቤቱ ተግባሮች በግብር መገለጥ እስኪጀምሩ ድረስ ይጠብቃል።

## 6. ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለዛሬው ትግል ከመቼውም ይበልጥ ያስፈልጋሉ።

የዲሞክራሲያዊ መብቶችን አስፈላጊነት እንደገና ለማጤን፣ ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸውን ሁኔታዎች ባንድነት አጣምረን፣ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታና አዝማሚያውም ወዴት እንደ ሆነ እንጠቁም።

ባንዱ በኩል የውስጥና የውጭ ፀረአብዮታዊ ሃይሎች በመጠናከር ላይ ይገኛሉ።በኤርትራና በጉረቤት አገሮች በኩል ያለው ሁኔታ፣ የኢምፔሪያሊዝም ሴራና የሁለቱ ሃያላን መንግስታት ውድድር፣ በሰሜንም ሆነ በደቡብ ኢትዮጵያ የነመንገሻ ስዩም — አሊ ሚራህ ፀረአብዮታዊ ግንባር መጠናከር፣ በከተሞች የቢሮክራሲው ሻጥር የመሬት ከበርቴዎች፣ የነፍጠኞችና የሌሎችም አድሃሪዎች ማንሰራራት፣ በተጨማሪም /ሳቦታዥ/፣ የንኡስ ከበርቴው ኩርፊያ፣ የወዛደሩ ገለልተኛነትና የሰራአጡ መብዛት፣ የንኡስ ከበርቴው ደንፊ ቡድን በተራማጅ ውስጥ ውዥንብርን መንዛት፣ እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ለፀረአብዮታዊ ቅልበሳ አመቺ ሆነው እናያለን።የኢትዮጵያ ህዝቦች በየካቲት እንቅስቃሴ ባቢያ ያገኙዋቸውን ድሎች ፀድቀዋል ለማለት ፈጽሞ አይቻልም።

ብዙ ተራማጆች በትክክል እንዳመለከቱት ሁሉ ''አብዮት በአብዮት ይሸራል''።ሰፊው ህዝብ ባልተደራጀበትና ባልታጠቀበት ባሁኑ ወቅት፣ ማእከላዊው ስልጣን ተገልብጦ በኢምፔሪያሊስቶች ሎሌዎች ከተያዘ፣ እነዚሁ ኢምፔሪያሊስቶችና ሎሌዎቻቸው ባጭር ጊዜ ውስጥ በሚልዩን የሚቆጠር ፀረአብዮታዊ ሰራዊት አሰልጥነው፣ አስታጥቀው ሊያሰልፉ ይችላሉ።በቬየትናም በዲዬም ጊዜ የሆነው አይነት ፀረአብዮት እዚህም ሊደረግ ይችላል።አሜሪካኖችና ዲዬም የመንግስትን ስልጣን ከጨበጡ ወዲያ፣ የቬየትናም ህዝብ ከፈረንሳይ ቅኝ ገዥዎችና ከጃፓን ፋሽዝም ጋር ተዋግቶ ያገኛቸውን ድሎች በሁለት አመታት ውስጥ ሙሉ በሙሉ፣ ለጊዜውም ቢሆን፣ ለመደምሰስ ችለዋል።ላራሹ የሆነውን መሬት መልሰው ቀምተዋል፤ ዲሞክራሲን አጥፍተዋል።

የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብም በፍጥነት እንዲነቃ፣ እንዲደራጅና እንዲታጠቅ ካልተደረገ፣ እስካሁን የተገኙት ድሎች ባጭር ጊዜ ውስጥ ሊደመሰሱ እንደሚችሉ ፈጽሞ መጠራጠር የለብንም።ይህ እንግዲህ የኢትዮጵያ የጊዜው ሁኔታ ጥቁር ገጽ ሲሆን ይህን አደጋ ለመቋቋም ዛሬ ከመቼውም ይበልጥ ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲፈቀዱ፣ ሰፊው ህዝብም በነርሱ እየተጠቀመ እንዲደራጅና ትግሉን በበለጠ እንዲያፋፍም ያስፈልጋል።ዛሬ የነዚህ የዲሞክራሲያዊ መብቶች መታወጅ ጉዳይ የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል በደረሰበት ደረጃ ፈጽሞ ሊቀር የማይችሉ ግዴታ ነው።እነዚህ መብቶች ካልተፈቀዱ የሰራተኛ ማህበራትንና የገበሬ ማህበራትን ማጠናከሪያ አዋጆችን ከስራ ላይ በትክክል ለማዋል አይቻልም።የቢሮክራሲውን፣ የኢምፔሪያሊዝምንና የውስጥና የውጭ አድሃሪዎችን ሴራ አጋልጦ እነርሱንም

ለመቋቋም አይቻልም::ስለዚህም፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶች የግድ መሰጠት ይኖርባቸዋል::እንደሚሰማው በእርግጥ የሚሰጡ ከሆነ እንግዲህ ጥያቄው የነዚህ መብቶች መሰጠት ምንን ያስከትላል? እኛንስ መብቶቹ በምን ይጠቅሙናል? የሚለው ነው::እነዚህን ጥያቄዎች ከመመለሳችን በፊት ግን አንድ ነገር:—

አንዳንድ የተሳሳቱ ተራማጆችና የዲሞክራሲያ አይነት አጋናባጆች ደርግ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ፣ ወይንም ደግሞ ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት'' የሚባለው ነገር እስካልተፈጠረ ድረስ፣ ወይንም ሰፊው ህዝብ የመንግስትን ስልጣን እራሱ እስካልጨበጠ ድረስ ምንም ዲሞክራሲ ሊኖር አይችልም ይላሉ::ይህ መቼስ ከታሪክ ቁስአካልነት የራቀ አስተሳሰብ ነው::በርግጥ የዲሞክራሲ ጉና ጥያቄ፣ ''አንገብጋቢ'' የመንግስት ስልጣን ጉዳይ ነው::ይህንንም ማለት የመንግስትን ስልጣን የያዘው መደብ፣ እንደመደቡ አይነት ዲሞክራሲውም ይለያል ማለት ነው::የቡርዧ ዲሞክራሲ የቡርዧው /የከበርቴው/ መደብ ፈላጭ ቆራጭነት ነው፤ አዲሱ ወይንም ብሄራዊ ዲሞክራሲም የሰፊው ህዝብ ፈላጭ ቆራጭነት ነው::ይሁንናም፣ ሰርቶአደሩ ህዝብ የራሱን ዲሞክራሲ ለመመስረት በስልጣን ላይ ካሉት መደቦች የመሰብሰብን፣ የመደራጀትን፣ የንግግርንና የጽሁፍን፣ ወዘተ. መብቶች ለማግኘት ይታገላል::እነዚህን አግኝቶም ለመንግስት ስልጣን ከውድድር ውስጥ ይገባል::ገና ለገና የመንግስትን ስልጣን አልያዝምና፣ የሚገኘውም ዲሞክራሲ ዘላቂነት አይኖረውምና ይህንን ስልጣን ከያዘው መደብ ወይም ከያዙት መደቦች በትግሉ የሚያገኘው ዲሞክራሲ አይጠቅመውም ማለት አይደለም:: ወይንም ደግሞ ስልጣንን እራሱ ካልጨበጠ፣ ታግሎ የሚያገኛቸው እነዚህ መብቶች ''ዲሞክራሲ'' አይደሉም ለማለት አይቻልም::እነሌኒን፣ ከሁሉ አስቀድሞ ለዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የታገሉት፣ በዚህ ሪፐብሊክ ውስጥ የሰፊው ህዝብ ዲሞክራሲ ይሰፍናል ብለው ስላመኑ ሳይሆን፣ ሪፐብሊኩ ለወዛደሩና ለሰርቶአደሩ ህዝብ ትግል፣ ሰፊውን ህዝብ ስልጣን ለማስያዝ፣ አይነተኛ መሳሪያ ነው ብለው ስላመኑ ነው::ይህም ደግሞ ታሪክ በገቢር እንዳረጋገጠው ሁሉ ትክክለኛ አስተሳሰብ ነበር::በዛሬይቱ ኢትዮጵያም የመንግስት ስልጣን ገና በሰፊው ህዝብ እጅ አልገባም::ሰፊው ህዝብ በትግሉ ከደርጉ በሚያገኛቸው ዲሞክራሲያዊ መብቶች በመጠቀም፣ የራሱን መንግስትና ዲሞክራሲ የሚመሰርትበትን አብዮታዊ ሁኔታ ይፈጥራል::

እንግዲህ ወደላይኛዎቹ ጥያቄዎቻችን እንመለስ:— የዲሞክራሲያዊ መብቶች መገኘት ምንን ያስከትላል? በነዚህ መብቶች እንዴት ልንጠቀምባቸው እንችላለን.

በዚህ ጋዜጣ ተደጋግሞ እንደተመቀሰው ሁሉ፣ ኢትዮጵያ መቼውንም ቢሆን ግልጽ የፖለቲካ ትግልን አይታ አታውቅም::ህብረተሰባችን በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም የታፈነ ስለነበር፣ አሁንም በቀላሱ ጉደል ሁኔታው እንደዚያው ስለሆነ፣ መደቦች ባደባባይ ወጥተው በጋዜጦች፣ በንግግሮችና በተለይም በየራሳቸው የፖለቲካ ድርጅቶች አማካይነት የታገሉበት ወቅት አልነበረም::ስለዚህም የመደቦች ትግል ይካሄድ የነበረው መደቦቹን በሚወክሉ አንዳንድ ግለሰቦችና የጥቂት ሰዎች ቡድኖች ዙሪያ ሆኖ፣ የትግሉም ዘዴ በወሬ፣ በሃሜት፣ በተንኮል/በኢንትሪግ/ ነበር::የዲሞክራሲያ ሰዎች የጋረሩት ፊውዳላዊ የፖለቲካ ትግል ዘዴ መሆኑ ነው::ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሲፈቀዱ መደብ ከመደቡ ይሰለፍና ባደባባይ ይወጣል::ባሁኑ ጊዜ በዝቅተኛ ደረጃ ተደራጅተው የሚገኙት የህዝብ ክፍሎች ሁሉ—ደርግም፣ ሰራዊቱም፣ ተማሪና ዘማቹም፣ ብሄረሰቡም፣ ሴቱም፣ ሰራተኛውም፣ ባጠቃላይ በህዝባዊ ድርጅቶችም ሆነ በሌላ መልክ የተደራጁት ክፍሎች — ይከፋፈላሉ::ሁሉም በየፖለቲካ መስመሩ፣ ማለትም ዙር ዙር በየመደቡ ይሰለፋል::የመደቦቻችንም አሰላለፍ ግልጽ ይሆንና ማን ከየትኛው ወገን እንደሆነ ይታወቃል::ይህም ትግሉን ያፋፍመዋል፤ የሰፊው ህዝብ ወገኖች ባንድነት የሚሰበሰቡበትን ሁኔታ ይፈጥራል::

ዲሞክራሲያዊ መብቶች ከተፈቀዱ የሰፊው ህዝብ የመፍጠር ችሎታ /ክሪኤቲቪቲው/ በነፃ ይለቀቃል::ማለትም ሰፊው ህዝብ አዳዲስ የድርጅት አይነቶችን፣ አዳዲስ የአሰራርና የምርት ዘዴዎችን፣ አብዮታዊ አካባቢዎችን በያለበት ይፈጥራል::በፊውዳሊዝሙ ስርአትና በኢምፔሪያሊዝም ተተብትቦ ተይዞ የነበረው ጉልበቱ ይፍታታል::ይህም አብዮቱን በቁስአካላዊም ሆነ በመንፈሳዊ ይዘቱ አሁን ካለው ሁኔታ አጥፍ—ድርብ ወደፊት ይገፋተረዋል::

ሰፊው ህዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ካገኘ አብዮታዊ አስተሳሰብን ባጭር ጊዜ ውስጥና በሰፊው ለማሰራጨት ይቻለናል:: ይህ ጋዜጣችን ወይንም እርሱን የመሰሉ ጋዜጦች አሁን ያላቸውን ስርጭት በአስር በሃያ እጅ ሊጨምሩ ይችላሉ:: በዚህም መንገድ ሰፊው ህዝብ በሃያ በሰላሳ አመታት ውስጥ ያላገኛቸውን የፖለቲካ ትምህርቶች በወራት ውስጥ ያገኛቸዋል:: ስለዚህም፣ አሁንም አብዮታዊ ሁኔታው በፍጥነት ያድጋል::

እንደሰሀዱ ያለው ጋዜጣ አብዮታዊ አስተሳሰብን የሚያሰራጭ ብቻ ሳይሆን፣ አደራጅም ነው:: ማለትም ጋዜጣው በያዛቸው አስተሳሰቦችና መፈክሮች ዙሪያ ግለሰቦችና ቡድኖች እንዲሰበሰቡ፣ ጋዜጣው መሰብሰቢያቸው እንዲሆን፣ የየእለቱን የትግል ዘዴ ሊያስተጋባ የሚችልና የወደፊቱንም አቅጣጫ ሊያነቃቸው የሚችል አይነተኛ መሳሪያ ይሆናል::

ባጭሩ፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሲኖሩ፣ ሰፊው ህዝብ ባጭር ጊዜ ውስጥ ሊማርና ሊደራጅ፣ ፊውዳሊዝምን፣ ኢምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን በይፋ ሊያጋልጥና ሊዋጋ፣ በመቀላላው የመደቦች ትግል እንዲፋፋምና ሰልፉ እየለየ እንዲሄድ፣ በዚያውም ህብረተሰባችን በውስጡ የያዛቸው አዳዲስ ወጣትና ገስጋሽ ሃይሎች ብቅ እንዲሉ ጥሩ አካባቢ ይኖራል::

ይሁንናም፣ ይህ ሁሉ ነገር በቀላሉ ከሰማይ እንደመና ይወርድልናል ብለን መጠበቅ የለብንም:: የዲሞክራሲያዊ መብቶች መኖር ለሰፊው ህዝብ ወገኖች እጅግ አስፈላጊ ነገር ቢሆንም፣ አድሃሪዎችና ኢምፔሪያሊስቶች መብቶችን ለማክሸፍ መብቶቹ በሚሰጡዋቸው ፍንጮች አይጠቀሙም ማለት አይደለም:: በተቻላቸው መንገድ ሁሉ ልዩ ልዩ ሻጥሮችን ከመፈፀም አይመለሱም:: ጥቂት ግለሰቦችንና ቡድኖችን በገንዘብ እየገዙ፣ በርከት ያሉ ድርጅቶችን የግራ ካባ አሰደርበው እያቋቋሙ፣ ተራማጁ እራሱ የበለጠውን እንዲከፋፈልና ትግሉን በነርሱ ላይ በማተኮር ፈንታ እርስ በርሱ እንዲጋጭ እያደረጉ፣ በሰፊው ህዝብ ውስጥ መቀላቀል ውዥንብርንና ውካታን ለመፍጠር ይችላሉ:: ዛሬ የሚታየውን የኢ.ህ.አ.ፓ. አይነት አወናባጅ ቡድኖች በብዛት ሊፈጥሩ ይችላሉ:: በነዚህ ላይ መንቃትና ተገቢውን ማጋለጥ ማከናወን የሃቀኛ ተራማጆችና የሰፊው ህዝብ ፈንታ ነው:: በተረፈም፣ ወታደራዊው መንግስት እራሱ በዲሞክራሲ የሚያምንና የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል ወደግቡ እንዲያመራ የሚመኝ ከሆነ፣ በኢምፔሪያሊስት አገሮች ሰላዮችና አወናባጆች ላይ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል::

አሁን ባለንበት ሰአት ሰፊ የፖለቲካ ክርክር ካለመደረጉ የተነሳ፣ የመስመር ትግል ይህን ያህልም የተፋፋመ ስላልሆነ፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሚመጡበት ጊዜ የግራው ሃይል በብዙ ትናንሽ ቡድኖች የተከፋፈለ ሆኖ ሊገኝ ይችላል:: ይህ ሁኔታና ከላይ የተጠቀሰው የአድሃሪዎች ሴራ ደርጉንም፣ ሰራዊቱንም፣ ፖሊሱንም ሊያስበረግግ ይችላል:: ስለዚህም፣ ባንድ በኩል ሀቀኛ ተራማጆች ባንድነት እንዲሰበሰቡ መጣር ሲኖርብን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ አይነቱ ሁኔታ የሚጠበቅና ቢኖርም ደግሞ ለመሸጋገሪያ ጊዜ እንጂ ዘላቂ አለመሆኑን በቅስቀሳችን ማስረዳት አለብን::

የዲሞክራሲያዊ መብቶች መታወጅ ለኢትዮጵያ ህዝቦች አዲስ አብዮታዊ ምእራፍን ይከፍታል:: በነዚህ መብቶች በመጠቀም ለጊዜው የሚታየውን የአድሃሪዎች መንሰራራት ለማጨናገፍ፣ እንደጥቁር ደመና ባገራችን ላይ የሚያንዣብበውን ፀረአብዮት ለመበታተንና ብሩህ የሆኑ ቀኖች እንዲመጡ ለማድረግ ይቻላል:: የኢትዮጵያ ህዝቦች የወደፊት እድል የጠራ ነው:: ለነዲሞክራሲያ፣ ለነመንገሻ ስዩምና ለሌሎቹም አድርባዮችና አድሃሪዎች ያገሪቱ ሁኔታ ጨለማ ሆኖ ይታያቸዋል:: ደርግ አገሪቱን ''ከአዘቀት ውስጥ ጨምሮአታል''፣ ስለዚህም ከአዘቀቱ የሚያወጣት የነርሱ ተአምረኛ ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት'' ብቻ ነው ይላሉ:: የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ግን በተጨባጭ [illegible] የነርሱ ብርሃን ለርሱ ጨለማ መሆኑን ያውቃል:: በበኩላችን የኢትዮጵያ የወደፊት እድል ከቀን ፀሃይ የጠራ ነው እንላለን:: የኢትዮጵያ ህዝቦች ነቅተው፣ ተደራጅተውና ታጥቀው፣ እንደአንድ ሰው ሆነው መነሳታቸውና ሶስቱን ጠላቶቻቸውን፣ ፊውዳሊዝም — ኢምፔሪያሊዝም — ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን መደምሰሳቸው ፈጽሞ አይቀርም:: በነርሱም መቃብር ላይ አዲስ ህዝባዊት ኢትዮጵያን ይገነባሉ:: የሚመጡት ቀናት የሰፊው ህዝብ ይሆናሉ::

## 7. መደምደሚያ፡- ተግባራችን

በየካቲት 1966 የተጀመረው የኢትዮጵያ ህዝቦች ሰፊ አብዮታዊ እንቅስቃሴ እየጎለበተ እ
የተነሳ፣ ብዙ መሰናክሎችን ተራ በተራ፣ ደረጃ በደረጃ እያሸነፈ፣ አሁን በጣም አመቺ ከሆነ ሁ
ኔታ ላይ ደርሶአል::በትግሉ ውስጥ ብዙ ተራማጆች፣ ብዙ የሰርቶአደሩ መደብ አባሎችና ጓዶች
ህይወታቸውን ጭምር መስዋእት አድርገዋል::አሁን በደረስንበት ደረጃ ከነርሱ እጅ የወደቀውን ባ
ንዲራ አንስተን፣ አርአያቸውን በመከተል፣ ቆርጠን በመነሳትና ማንኛውንም መስዋእትነት ሳንፈራ፣
የሚመጡትን ችግሮች ሁሉ አንድ ባንድ እያሸነፍን ወደፊት መገስገስ አለብን::

ሰሀዴ ትክክለኛ የፖለቲካ መስመር አለው::ከአድሃሪያቸ፣ ከቀኝና ከግራ አድርባዮች ጋር
እየታገለ በሂደ ቁጥር ደግሞ ይህ መስመራችን የበለጠውን እየጠራ ይሄዳል::ነገር ግን፣ የአብዮ
ቶች ታሪክ እንደሚያስተምረን ሁሉ፣ ትክክለኛ መስመርን መያዝ በራሱም አይነተ ብቻውን አይበቃም::
ይህ መስመር በሰፊው ህዝብ ውስጥ መሰራጨት አለበት::በድርጊትም መተርጎም አለበት::ስለዚህም
የሰሀዴ ሰዎችና ደጋፊዎቹ ሁሉ ተያይዘን መጠንከር፣ መስፋፋት አለብን::በየትምህርት ቤቱ፣ በየ
ፋብሪካው፣ በየመስሪያ ቤቱ፣ በየከተማውና በየገጠሩ፣ በተቻለ ቦታ ሁሉ የጋዜጣችን አንባቢ ቡድ
ኖች መቋቋም አለባቸው::ሰሀዴን በሰፊው ማሰራጨትና የያዘውን መልእክት በቃልም ቢሆን ማስተላለፍ
ግዴታችን ነው::ያንባቢ ቡድኖችም ጋዜጣውን ባገኙበት መንገድ በሙሉ እንዲጽፉልን፣ እንዲያርሙን፣
አዳዲስ አሳቦችን እንዲያቀርቡልን መደረግ አለበት::ትክክለኛ መስመራችን በሰፊው ህዝብ ውስጥ
ካልገባ፣ ከሰፊው ህዝብ እርዳታና ትምህርት ካላገኘን፣ ሰፊው ህዝብም ይህንን መስመር የራሱ አ
ድርጎ ካልወሰደ ስራችን ዋጋ አይኖረውም::

ለዲሞክራሲያዊ ትግል ካሁኑ መዘጋጀት አለብን::ይህ ትግል አሁን የያዝነውን ስራ እጥፍ
ድርብ እንደሚያደርገው መገንዘብና በቁስአካላዊ ሆነ በመንፈሳዊ አቋማችን እንድንጠነክር የተቻ
ለውን ሁሉ ጥረት ማድረግ አለብን::የሰሀዴ ሚሊታንቶችና ደጋፊዎች በያለበት እንዲበዙ፣ በስራው
እንዲበረቱ፣ ሰፊ ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ እንዲያደርጉና የጊዜውን ድክመታችንን ወደጥንካሬ እንድንለ
ውጠው በሃይል መታገል ያስፈልጋል::እንግዲህ፣ ለዚህ ተግባራችን የቅስቀሳችንና የፕሮፓጋንዳችን
ይዘት ምን ይሆናል?

1ኛ/ ኤርትራንና ጎረቤት አገሮችን በሚመለከተው በኩል፣ ባሁኑ ሰአት ያለውን አደጋ ለ
ህዝቡ መግለጽ አለብን::ሰሀዴ ብሄረሰቦች የራሳቸውን እድል የመወሰን መብት እንዳላቸው ያውቃል::
የኤርትራ ብሄረሰቦችም ሆኑ ሌሎች ብሄረሰቦች የገዛ እድላቸውን እንዳሻቸው ለመወሰን መብት አላ
ቸው::ይሁንናም፣ የኤርትራን ግንባሮች አድርባይነትና በነርሱም ሳቢያ የመጣውን የጎረቤት አገር
ችንና የሃያላን መንግስታትን ጣልቃገብነት ማጋለጥ አለብን::የኤርትራና የኢትዮጵያ ህዝቦች ችግ
ሮቻቸውን በራሳቸው ለመፍታት ይችላሉ::በኤርትራ በኩል ያለውን አደጋ የኤርትራ ተራማጆች ተገን
ዝበውት አብረን እንድንገሰፍ ጥሪ እናደርግላቸዋለን::በግለሰብ ደረጃም ሆነ በድርጅት፣ በአገር
ውስጥም ሆነ በውጭ አገር፣ የኤርትራንና የሌሎችንም ክፍሎች ብሄረሰቦችን ኢንተርናሽናሊስቶች ለ
ማደራጀት መጋበዝ አለብን::በወዛደሩ ርእዮተአለም ላይ የቆመ የወዛደሩን ፓርቲ ለማቋቋምና ለመገ
ንባት የምንችልበትን መንገድ ማግኘት ያስፈልገናል::ሰሀዴ ጠባብ ብሄርተኝነትንና የትልቅ ብሄረ
ሰብ ትምክህትን ይቃወማል፣ ይዋጋል::

2ኛ/ የነኢ.ዲ.ዩንና የሌሎችንም አድሃሪያቸ ፕሮፓጋንዳና ከኢምፔሪያሊዝምና ከቢሮክራሲ
ያዊ ከበርቴው ጋር የሚያደርጉትን ሴራ ማጋለጥ አለብን::የነዚህን ፀረአብዮታዊ መፍጨርጨር የሚ
ደመስሰው የሰፊው ህዝብ መንቃት፣ መደራጀትና መታጠቅ ነው::ሰፊው ህዝብ ነቅቶ፣ ተደራጅቶ መታ
ጠቅ አለበት::ኢትዮጵያን ከውጭ ወረራና ከፀረአብዮታዊ ቅልበሳ ሊያድናት የሚችል የተደራጀና የ
ታጠቀ የህዝብ ሃይል ብቻ ነው::ሌላ የለም::

3ኛ/ የደርጉን የመደብ አቋምና በውስጡ ያሉትን የቀኝና የግራ ተገሎቹን፣ ሰፊው ህዝብ
እንዲገነዘባቸው ማድረግ አለብን::ከደርግ ወደገጠር እየተላኩ በሰፊው ህዝብ ላይ ፋሽስታዊ ወን
ጀሎችን የሚፈጽሙትን የቀኝ ሰዎች ህዝቡ ራሱ ያውቃቸዋል::እነዚህን የኢትዮጵያ ህዝብ ይፋረዳቸ
ዋል::ባጠቃላይ ሲታይ ግን ደርግ ባሁኑ ሰአት የኢትዮጵያ ህዝቦች ዋና ጠላት አይደለም::ነገ
ሊለወጥ የሚችል ጊዜያዊ ወዳጅ ነው::ስለዚህም በርሱና በፊውዳሊዝም–ኢምፔሪያሊዝም–ቢሮክራሲያዊ
ካፒታሊዝም መካከል ያሉትን ቅራኔዎች ማባባስና ይበልጡ የደርግ አባል ከሰፊው ህዝብ ጎን እንዲ
ሰለፍ ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ማድረግ አለብን::በማንኛውም መንገድ ፊውዳሊዝም–ኢምፔሪያሊዝምና ደ
ርግ ''አንድም–ሶስትም'' አይደሉም::

4ኛ/ የተራማጆችን አሰላለፍ በሚመለከተው በኩል፣ ዋናው አላማችን በወዛደሩ ርእዮተአለም
ላይ የቆመና ሃቀኛ ተራማጆችን ያቀፈ የወዛደር ፓርቲ መፍጠር ነው::ለዚህም ባንድ በኩል በጥናት
ቡድኖች አብዮታዊ ቲዎሪን ማስፋፋትና ጥራዝ–ነጠቅነትን መቋቋም፣ በኛ መስመር ባጠቃላይ ከሚስማሙ
ሌሎች ቡድኖች ጋር መቀራረብና ያሉትንም ልዩነቶች በሂስና በግለ ሂስ ማሸነፍ፣ በሌላ በኩል ደግሞ
ከ''ግራ'' አድርባዮች ጋር የሃሜት ሳይሆን ጠንካራ የርእዮተአለም ትግል ማካሄድ አለብን::
የህዝቡን መንቃት፣ መደራጀትና መታጠቅ የሚቃረነውንና የንኡስ ከበርቴውን ፈላጭቆራጭነት በኢትዮ
ጵያ በአዲሱ ለመመስረት የመጣውን ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት'' የሚለውን መፈክር ፋርሽነት
በሰፊ ውይይት ማሳየት ይገባናል::

እንግዲህ፣ ጓዶች፣ ጊዜው ጥሩ ነው! ወደፊት!!

ሰፊው ህዝብ ያሸንፋል!!!